# መመሪያ-ደንብ

**ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

**ከዚህ ጋር አግባብ ያላቸው/የሚዛመዱ፦** JPA-RA
**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፦** ዋና የአካደሚ ኃላፊ
ዋና የሥራ ሀላፊ

## ደህንነት እና የማጣራት ምርመራ ፕሮግራሞች፦ Lead/ሊድ፣ መስማት፣ እና እይታ

I. **ዓላማ**

ተማሪዎች ከ lead መርዛማነት ስጋት ነፃ መሆናቸውን ለመለየትና ለማረጋገጥ የስቴት እና የፌደራል መስፈርቶችን ለማሟላት።

የስቴት መስፈርቶችን ለማሟላት ተማሪዎች ከመስማት እና ከማየት ችግር ነጻ መሆናቸውን ለማጣራት እና ለማወቅ፣ የመስማት እና የማየት ጉድለት ያለባቸውን ልጆች ለማስተላለፍ እና ለመከታተል፣ እና የማጣራት ውጤትን አግባብ ላላቸዉ ግለሰቦች መተርጎም።

የስቴት እና የፌደራል መመሪያን ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት ቤት እና የቢሮ የመጠጥ ውኃ ጤናማና ንጹህ መሆኑን ማረጋገጥ።

II. **የበፊት መነሻ/አመጣጥ**

የማጣሪያ ሂደቶች የሕፃናት አጠቃላይ የጤና አያያዝ አካል ናቸው። ይበልጥ የጤና ምርመራ/ክትትል የሚያስፈልጋቸው ልጆችን ለይቶ ለማወቅ የሚቻለው በመምህር ምልከታ-ትኩረት፣ የጤንነት ታሪክ፣ የማጣራት ምርመራ፣ እና የህክምና እና በስነልቦናዊ ምዘናዎች እና ምርመራ ነው።

ለሊድ/Lead በመጋለጥ ምክንያት በሊድ/Lead መመረዝ በስፋት ያለ የአካባቢ ብክለት አደጋ ነዉ። ህፃናት ከመወለድ ጀምሮ እስከ ስድስት ዓመት እድሜ የነርቭ እድገት ሂደት ላይ ባሉበት ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ሊጠቁ ይችላሉ። lead የተሰኘ መርዛማ ጋዝ ለረዥም ጊዜ መጋለጥ የረዥም ጊዜ የነርቭ ጉዳት እና ሞት ሊያስከትል ይችላል። በአካባቢያችን ውስጥ ላለ ሊድ/lead መጋለጥ የሚያስከትላቸው ውጤቶች የመማር ስንክልናን፣ በአንክሮ መከታተል ያለመቻል፣ መኮስኮስ፣ እና IQ (የአእምሮ ብሩህነትን) መቀነስን ያካትታል።

የመስማት እና የማየት ችግሮች የጤና ችግሮች ከመሆናቸውም በላይ ለመማር መሰናክል ሊሆኑ ይችላሉ። ማጣራት ሲደረግ በቅድሚያ ችግሩን ለማወቅ ያስችላል።

III. **ትርጓሜዎች**

A. በሊድ/Lead መመረዝ የማጣሪያ ምርመራማለት ተከታታይ ጥያቄዎችን ከሊድ አደጋ መጠይቆች በመጠየቅ እና/ወይም የደም ናሙና በመዉሰድ ምን ያክል Lead ደም ዉስጥ መኖሩን ምርመራ በማካሄድ የ Lead መመረዝ ስጋትን ለማወቅና ለማረጋገጥ በጤና ባለሙያዎች የሚካሄድ ስልት/ስትራቴጂ ነው።

B. ስጋት ያጠላበት አካባቢ ማለት በሜሪላንድ የጤና መምሪያ (MDH) አማካይነት ልጆች Lead ሊመረዙ ይችላሉ የሚል ስጋት እንዳለበት በተለይትኩረት የተደረገበት አካባቢ ነው። ከጃኑዋሪ 1/2015 በፊት

ለተወለዱ ህፃናት የአስጊ አካባቢዎች በሜሪላንድ የጤና መምሪያ እና የአእምሮ ሃይጂን (DHMH) Blood Lead Testing Certificate, DHMH 4620 (DHMH Form 4620) በደም የሊድ ምርመራ ሰርትፊኬት ተለይተው ይታወቃሉ። ከማርች 26/2016 ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ ከጃኑወሪ 1/2015 በኋላ ለተወለዱ ልጆች አስጊ አካባቢዎች መሆናቸውን በሜሪላንድ የስጋት አካባቢዎችን ትኩረት የማድረግ እቅድ፣ ኦክቶበር 2015/Maryland Targeting Plan for Areas at Risk for Childhood Lead Poisoning, October 2015 (2015 Targeting Plan) በሜሪላንድ ስቴት በሁሉም ዚፕ ኮድ ተለይተው ይታወቃሉ።

IV. **ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች**

A. የ Lead መርዛማነትን/የሊድ ብክለትን ማጣራት

1. ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለሚገቡ ተማሪዎች ቅድሚያ ጀማሪዎች/Head Start ወይም ለአጠቃላይ ቅድመ-ሙዓለህፃናት፣ከፌደራል እና ከስቴት መስፈርቶች ጋር በሚጣጣም መልኩ ተማሪው(ዋ) የደም ምርመራ እና/ወይም የ lead መመረዝ የማጣራት ሂደት የጨረሰ/ች ስለመሆኑ/ኗ የሚያረጋግጥ DHMH Form 4620 መሞላት አለበት።

2. ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ልዩ ትምህርት ቅድመ-መደበኛ ትምህርት ፕሮግራሞች/MCPS special education pre-school programs፣ ሙዓለህፃናት ወይም አንደኛ ክፍል፣ለሚገቡ ተማሪዎች ከስቴት መስፈርቶች ጋር መሚጣጣም መልኩ DHMH 4620 መሞላት አለበት።

   a) ልጁ/ልጅቱ የተወለደ(ች)በት ቀን ከጃኑወሪ 1/2015 በፊት ከሆነ፣ እና በሜሪላንድ DHMH Form 4620 ላይ በተገለጸው ስጋት በሚታይበት አካባቢ ካልኖረ/ች፣ ወላጅ/ሞግዚት ልጁ(ልጅቱ) ስጋት ባለበት አካባቢ ያልኖረ/ች መሆኑን የሚያረጋግጠውን የ DHMH Form 4620 ክፍል ይሞላሉ።

   b) ከማርች 28/2016 ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለ፣ ልጁ/ልጅቱ ከጃኑወሪ 1/2015 በኋላ የተወለደ/ች እና በሜሪላንድ 2015 የትኩረት ፕላን ተለይቶ የሚታወቅ ስጋት ያለበት አካባቢ አሁን እየኖረ(ች) ወይም ቀደም ሲል መኖሩ(ሯ) የሚታወቅ ከሆነ፣ የልጁ/ጅቷ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ የ DHMH Form 4620 በመሙላት (ወይም የልጁ/ጅቷ የደም ሊድ ምርመራ ትንታኔ ኤሌክትሮኒካዊ ዘገባ)፣ ልጁ/ጅቷ በ 12 ወር ጊዜ ውስጥ እና በድጋሚ በ 24 ወራት ጉብኝት ወቅት መመርመርን እና /ወይም ለሊድ መርዝ የደም ምርመራ መከናወኑን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች።

   c) ከማርች 28/2016 ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ፣ የ24 ወር ወይም የሚበልጥ እድሜ ያለዉ/ላት ልጅ እና ከ6 ዓመት የሚያንስ እድሜ ያለዉ/ላት ልጅ ስጋት ባላበት አካባቢ እየኖረ/ች ያለ/ች ወይም ቀደም ሲል በዚያ አካባቢ መኖሩ/መኖሯ የሚታወቅ ከሆነ፣ የልጁ/ጅቷ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ስለ lead መመረዝ የደም ምርመራ ማድረግ አለበት/ባት፣ ይኼውም፡-

      (1) ልጁ/ልጅቱ ከዚህ በፊት ስለ lead መመረዝ የደም ምርመራ አልተደረገለ(ላ)ትም፤ ወይም

      (2) የልጁ/የልጅቱ ወላጅ/ሞግዚት ስለ lead መርዛማነት የደም ምርመራ ለልጁ/ለልጅቱ የተደረገለ(ላ)ት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሠርተፊኬት ለማቅረብ ካልቻሉ፣ ወይም

      (3) የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ባለሙያ ከዚህ በፊት የተደረገ የlead የደም ምርመራ ውጤት ለማግኘት አልቻለም/አልቻለችም።

d) በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት ኦክቶበር ላይ፣መስፈርቱን ተግባራዊ ላላደረጉ ለልዩ ትምህርት ቅድመ ሙአለህፃናት፣ መዋእለህፃናት፣ እና 1ኛ ክፍል ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች ከትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች (SHS) የክትትል ደብዳቤ ይሰጣቸዋል። በደብዳቤው ላይ መጠቀስ ያለበት ወላጅ/ሞግዚት ስለ ልጃቸው lead የደም ምርመራ ሠርተፊኬት ወይም DHMH Form 4620 with Box C (religious exemption) በኃይማኖት ምክንያት የታለፈ መሆኑን ተሞልቶ የተፈረመበት ቅጽ ማቅረብ እንዳለባቸው በህግ የተደነገገ መሆኑን ይገልጻል።

B. የመስማት እና የማየት ምርመራ

1. ወደ MCPS 1ኛ ክፍል፣ እና 8ኛ ወይም 9ኛ ክፍል የሚገቡ እና ተመሣሣይ እድሜ ክልል ላይ የሚገኙ የልዩ ትምህርት ተማሪዎችን በሙሉ ባለፈው ዓመት ተማሪው(ዋ) optometrist ወይም ophthalmologist ምርመራ የተደረገለ(ላ)ት መሆኑን ማስረጃ ካላቀረቡ በስተቀር የመስማት እና የማየት ማጣራት ምርመራ ለማድረግ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ነርስ (SCHN) እና ርእሰመምህር እቅድ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለባቸው። እንዲሁም የመስማት እና የማየት ችግር ምልክት የሚታይባቸው የተመሩ/የተላለፉ ተማሪዎችም ምርመራ ይደረግላቸዋል።

2. ማጣራቱ የሚካሄደው በትምህርት ቤቶች ነው። የመስማት እና የማየት የማጣራት ምልመላ ለማድረግ በተቻለ መጠን ፀጥታ የሰፈነበት ክፍል የመስማት ምልመላ/ማጣራት ለማድረግ እና የማየት ችሎታን ለማጣራት እንደ አስፈላጊነቱ አመቺ የሆነ ቦታና በቂ ብርሃን ያለበት ክፍል መሰጠት አለበት። የማጣራቱ ተግባር የሚጠናቀቀው በትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች የመስማት እና የማየት አጣሪ ቡድን አባላት አማካይነት ይሆናል።

3. የመስማት እና የማየት የማጣራት ምርመራ ውጤቶችን፣ በስቴት ህግ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ቁሳቁሶችን፣ እና ተማሪው(ዋ) የመስማት እና የማየት ማጣሪያ ምርመራዎችን ያላለፈ(ች) ከሆነ optometrist ወይም ophthalmologist ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግለ(ላ)ት አስተያየት የተሰጠበትን መረጃዎች እና ሌሎችም በስቴት ህግ የተደነገጉ ኢንፎርሜሽኖችን SCHN ለእያንዳንዱ ተማሪ ወላጅ/ሞግዚት ይልካል/ትልካለች። የመስማት እና የማየት ማጣሪያ ምርመራ ውጤቶች በተማሪ ሪኮርድ ካርድ 5 Health Screenings (MCPS Form SR-5) ላይ መቀመጥ ይኖርበታል፣ እና ለእያንዳንዱ ተማሪ ቋሚ የሪኮርድ አካል ይሆናል።

   SCHN ወዴት ማስተላለፍ እንደሚያስፈልግ የሚነሱ ጥያቄዎችን ይመልሳል ወይም ቤተሰብን እንደየአስፈላጊነቱ ከማህበረሰብ መገልገያዎች/resources ጋር ያገናኛል።

4. ወላጅ/ሞግዚት የማጣራቱ ሂደት ከሃይማኖታዊ እምነታቸው ጋር የሚጋጭ ነው ብለው ካመኑ ተቃውሞአቸውን በጽሑፍ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

5. SCHN የተገኘውን አይነተኛ ውጤት እንደአስፈላጊነቱ ከትምህርት ቤት ሠራተኞች ጋር ማጋራት ይችላል።

6. የትምህርት ቤት ሠራተኞች ለበለጠ የማጣራት ሂደት የት/ቤት የጤና ማኑዋል/School Health Manual (SHM) መከተል/ማየት አለባቸው።

## V. የመጠጥ ውኃ ጤንነት

A. የዩ.ኤስ. የአካባቢ ጥበቃ/እንክብካቤ ኤጀንሲ/U.S. Environmental Protection Agency (EPA) የትምህርት ቤቶችን የመጠጥ ውኃ ምርመራ ፕሮቶኮሎች እና ቅድሚያ ጥንቃቄ የቴክኒክ መመሪያዎችን ተግባራዊ በማድረግ MCPS የትምህርት ቤት የመጠጥ ውኃን ንፅህና ይቆጣጠራል። በተጨማሪ፣ MCPS

በሜሪላንድ የአካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ መምሪያ የተሰጡ መመሪያዎችን በማክበር በየጊዜው የመጠጥ ውኃ መውጪያዎችን/መፍሰሻዎችን በየሦስት - ዓመት ዑደት ስለንፅህና ምርመራ ያደርጋል።

B. የመጠጥ ውኃ ንፅሕናን ለመጠበቅ፣ የተዘረጉ የውኃ መስመሮችን ማሻሻል፣ የፍሳሽ ፕሮቶኮሎችን፣ እና የትምህርት ትጋትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ MCPS በስቴት እና በካውንቲ ደረጃ ከሚገኙ አጋር ኤጀንሲዎች ጋር ይሠራል።

C. የመጠጥ ውኃ ምርመራ ፕሮግራሞችን እና ውጤቶችን MCPS ለማህበረሰቡ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ያሳውቃል።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Code of Maryland Regulations §10.11.04.02, .04-.06; § 26.16.07 Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-404, Annotated Code of Maryland, Environment Article § 6-1501; U.S. Environmental Protection Agency (EPA) Technical Guidance for Testing Protocols

**የደንብ ታሪክ፡-** የቀድሞ ደንብ ቁ. 525-8፣ ኦክቶበር/1982 ከለሳ ተደርጓል፣ ኦክቶበር 2/2008 ከለሳ ተደርጓል፣ ኦገስት 13/2009 ከለሳ ተደርጓል፣ ኦክቶበር 17/2018 ከለሳ ተደርጓል።